July 21, 2007

# በክፉ ቀን ደራሽ !!

መቸም በአገር ጉዳይ
የለም ነበር ድሮ
አወዳሽ ተወዳሽ
ዘመን ተለውጦ
በሆነበት ጥቂት
በክፉ ቀን ደራሽ፡፡
በድቅድቅ ጨለማ
ብርሀን በጠፋበት
አንዲት ቁራጭ ሻማ
ፀሀይ በሆነበት፡፡
የቀን ስራ ድካም
የሌሊት መኻታ
እንቅልፍ ሳያምራችሁ
የወሬውን ግርዱን
ገለባ ገፋችሁ
ምርቱን በዌቫችሁ
ፖስት እያረጋችሁ
በአገር ወሬ ጥማት
ህዝብ ታሞ ራሱን
ቡና የሆናችሁ
ጥላቻ ያረገዘ
ውርጃ እያጣደፈው
አገር እንዳትደርሱ
ብሎክ ሲያረጋችሁ
በተሸበብንበት
አፋችን ሆናችሁ
ስንጮህም ደግሞ
ጆሮአችን ሆናችሁ

በዛ በክፉ ቀን
በድቅድቅ ጨለማ
አንዲት ቁራጭ ሻማ
ፀሐይ የሆናችሁ
ዌብ ሳይት አዘጋጆች
እንኳን ደስ ያላችሁ
ዌብ ሳይት ባለቤቶች
እንኳን ደስ ያላችሁ።
የእናንተን አሻራ
በትግሉ ጎራ
ማንም አይጋራ
በድንቅ ስራችሁ
ተነስቷል ተራራ።
ግና---አትዘናጉ
ተጀምሯል እንጂ
አላለቀም ወጉ።
መድህን የምትሆን
የሰላም አዝመራ
ፍሬ እንዳታፈራ።
የፍቅር አበባ
በእያንዳንዱ ጎጆ
ሆ! ብላ እንዳትገባ።
የአንድነት ውላችን
እንዲበጠስ ክሩ
ሌላው እየሞተ
እነሱ ሊኖሩ
እረ ጎራው ብለው
ተነስተው የሚያቅራሩ
እንዳያንሰራሩ
አፋችን ሆናችሁ
ከሀገር እስኪገፈፍ
ግፍና መከራ

ህዝቡ ላይ የሚወርደው
ሰቆቃ እስኪያባራ
ለሚያምኑት ነውና
የሚሰጥ አደራ
የክፉ ቀን ደራሽ
የመሆናችሁ ዕጣ
ነውና በእጃችሁ
ተመዞ የወጣ
እስኪወጡ ድረስ
ከድህነት ጎጆ--ጎስቋላ ልጆችዋ
ለእናት አገራችን
ሁኑ አፍ ጆሮዋ ፡፡

ስሜነህ መሸሻ
(ከላስ ቬጋስ)